የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን
ETHIOPIAN AGRICULTURAL BUSINESSES CORPORATION

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ኢግሥኮ)
አጭር መግለጫ/ፕሮፋይል

Ethiopian Agricultural Businesses Corporation (EABC)
Company Profile

የካቲት 2017 ዓ.ም
February 2025

ኮርፖሬሽኑ ያስገነባው የቦንጋ የተቀናጀ የግብርና ግብዓትና የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከል

ማውጫ/Contents ገጽ/Page

የኮርፖሬሽኑ ምስረታ..... 2
የተቋቋመበት ዓላማ..... 3
ተልዕኮ፣ ራዕይ እና እሴቶች 5
የግብርና ግብዓቶችና የእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦት
እና አገልግሎቶች..... 6
የዓመታዊ ሽያጭ፣ ትርፍና የተፈቀደ ካፒታል እድገት..... 13
ማኅበራዊ ኃላፊነት..... 13
እውቅና እና ሽልማት..... 16
አደረጃጀት..... 18
የዘርፎች አድራሻ እና የሚሰጡት አገልግሎት..... 19
Establishment of EABC 21
The products and services of EABC 25

አዘጋጅ:-

በኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የኮሚዩኒኬሽን
እና ማኅበራዊ ጉዳዮች አገልግሎት

የኮርፖሬት ኮሚዩኒኬሽን እና ማኅበራዊ ጉዳዮች
አገልግሎት ኃላፊ፡- ጋሻው አይችሉህም

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
ከተማ፡- አዲስ አበባ

ክፍለ ከተማ፡- አቃቂ ቃሊቲ
ወረዳ፡- 06
ቦታ፡- ወደ ቃሊቲ በሚወስደው መንገድ ከሆራይዘን አዲስ ጎማ ዝቅ
ብሎ አልያም ከፋፋ ምግብ አ/ማ 150 ሜትር ወደ ውስጥ ገባ ብሎ
ስልክ ቁጥር፡- ሞባይል 0911 67 77 54፣ የቢሮ +251-11424125
የመ.ሣ.ቁ፡- 6898

ኢሜይል፡ info@ethioagri.com or ethioagribusco@gmail.com
ዌብሳይት፡- www.ethioagri.com
ፌስቡክ፡- Ethiopian Agricultural Businesses Corporation

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ኢግሥኮ) አጭር መግለጫ/ፕሮፋይል

ምስረታ

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ኢግሥኮ) በግብርናው ዘርፍ ከ30 እስከ 40 ዓመት ድረስ በተናጠል አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ አምስት ነባር ድርጅቶችን (የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማኅበር፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ድርጅት እና የተፈጥሮ ሙጫ ምርትና ገበያ ድርጅት) በማዋሃድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 368/2008 መሠረት ታህሳስ 2008 ዓ.ም የተቋቋመ መንግሥታዊ የልማት ድርጅት ነው።

ተጠሪነት

በግሉ ዘርፍና በተደራጁ ማኅበራት የማይሸፈኑ የገበያ ክፍተቶች ውስጥ የድርሻውን በመውሰድ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማከናወን ላይ የሚገኘው ኮርፖሬሽኑ ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ሲሆን፣ በሥራ አመራር ቦርድ ይመራል።

የተቋቋመበት ዓላማ

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፦

፩/ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ገዝቶ ለገበያ ማቅረብ፤ ማዘጋጀት፤ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን የገበያ ዋጋ የማረጋጋት ተግባራትን ማከናወን፤

፪/ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የእርሻና የኮንስትራክሽን

መሣሪያዎችን የጥገና አገልግሎት፣ የእርሻ መሣሪያዎችንና የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን የኪራይ አገልግሎት በክፍያ መስጠት፤

፫/ የእርሻ መሣሪያዎችንና መለዋወጫዎችን፣ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን እና አግሮ ኬሚካሎችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ገዝቶ ለሽያጭ ማቅረብ፤

፬/ ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች አጠቃቀም እንዲለመድ አስፈላጊውን ትምህርት መስጠት፤ ስለ እርሻ መሣሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም የምክር አገልግሎት መስጠት፤ የቴክኒክ ሞያ ማሻሻያ ሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት፤

፭/ የተፈጥሮ ሙጫ ምርት መሰብሰብ፣ መግዛት፣ እሴት መጨመር፣ ማዘጋጀት፤ ሌሎች ከደን ውጤቶች የሚመረቱ ምርቶችን ማምረት፣ ለሀገር ውስጥና

ለውጪ ገበያዎች ማቅረብ፤

፮/ የእርሻ መሬት ልማት ጥናትና ዲዛይን፣ የእርሻ መሬት ቅየሳ፣ ምንጣሮና ማስተካከል፣ የውኃ ተፋሰስና የመስኖ ሥራ እንዲሁም ከእርሻ መሬት ልማት ጋር የተዛመዱ ሥራዎችን ማከናወን፤

፯/ የአዳዲስና ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን አዋጪነት ጥናት፣ የዲዛይን ዝግጅት፣ የቴክኖሎጂ መረጣና ድርድር፣ የተከላና የኮሚሽኒንግ እንዲሁም የምርምር ሥራዎች እንዲካሄዱ ማድረግ፤

፰/ አቅሙ ካላቸው የሀገር ውስጥ እና የውጪ ኩባንያዎች ጋር በመተባበር የግብርና የማምረቻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች ዲዛይንና የማምረት ሥራዎች በሀገር ውስጥ እንዲከናወኑ ማድረግ፤

፱/ ለመስኩ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የትምህርት፣ የምርምርና የሥልጠና ተቋማት ጋር በመተባበር መሥራት፤

፲/ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በሚሰጠው አቅጣጫ ላይ በመመስረት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ እገዛ የሚያደርጉለትን የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የዘመናዊ አስተዳደር ግብዓቶችን ለማግኘት የሚያስችለውን (ኢንቨስትመንት መሳብንም ሆነ በኢንቨስትመንት መሳተፍን ጨምሮ) ጥናት በማካሄድ ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፤

፲፩/ የተለያዩ የአዝዕርት፣ የአትክልት፣ የፍራፍሬና የመሳሰሉት ቅድመ መሥራች፣ መሥራችና የተመሠከረለት ዘር ማባዛት፣ ማበጠርና ማዘጋጀት፣ እንደ አስፈላጊነቱም ቅድመ መሥራች ዘሮችን ከውጭ አገር በማስመጣት ማስመረት ወይም መሸጥ፣ ተረፈ ምርቶችን ለገበያ ማቅረብ፤

፲፪/ በግብርና ግብዓት አቅርቦት፣ በእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦት፣ በእርሻ መሣሪያዎች ጥገና፣ በተፈጥሮ ሙጫ ምርትና ገበያ፣ በሜካናይዜሽን አገልግሎትና በተዛማጅ ሥራዎች ዙሪያ ምርምር በማካሄድ የተሻሻሉትን ተግባራዊ ማድረግ፣ በውጤቱም ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ፤

፲፫/ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በሚሠጠው አቅጣጫ መሠረት ቦንድ መሸጥ፣ ዋስትና ማስያዝ፣ ከሀገር ውስጥና ከውጪ የገንዘብ ምንጮች የብድር ውል መደራደርና ሲፈቀድ መፈራረም፤

፲፬/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማከናወን ናቸው።

የኮርፖሬሽኑ ተልዕኮ፣ ራዕይ እና እሴቶች

ተልዕኮ

ለግብርና ምርትና ምርታማነት ዕድገት አስተዋጽዖ የሚያደርጉ፣ ለዘመናዊ እርሻና ለአግሮ ኢንዱስትሪ መስፋፋት መሠረት የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እና ግብዓቶችን ተደራሽ በማድረግና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ሀገራዊ ልማትና ዕድገትን ማፋጠን።

ራዕይ

በግብርና ግብዓት አቅርቦት እና በሜካናይዜሽን አገልግሎት በ2022 ዓ.ም በአፍሪካ ተወዳዳሪ ተቋም መሆን።

እሴቶች

- ተዓማኒነት
- ግልጽነት
- ቅንነት
- ቁርጠኝነት
- የጋራ ተጠቃሚነት
- ማኅበራዊ ኃላፊነት

የአንድ መስኮት አገልግሎት

የአንድ መስኮት የተቀናጀ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘው ኮርፖሬሽኑ፣ በተቀናጀ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ከመሬት ዝግጅት እስከ ጎተራ የሚዘልቁ የግብርና ሥራዎችን ያከናውናል። በተጨማሪም ለግብርና መዘመንና ለምርታማነት እድገት የላቀ አስተዋጽዖ ያላቸውን ግብዓቶች (ምርጥ ዘር፣ ጠጣርና ፈሳሽ ማዳበሪያዎች፣ አግሮኬሚካሎች) እንዲሁም የእርሻ መሣሪያዎችን ከእነተቀጽላቸው እና መለዋወጫቸው በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚዎች ያቀርባል።

ከዚህ ባሻገር ኮርፖሬሽኑ ለደንበኞቹ እየሰጠ የሚገኘውን የአንድ መስኮት አገልግሎት የተሟላ ለማድረግ የምክር፣ የቴክኒክና ሞያ ሥልጠና፣ የዘር ብጠራ፣ የደረቅ ጭነት ትራንስፖርት እና የተሽከርካሪዎች ጥገና አገልግሎቶችን በዋና መ/ቤት እና በቅርንጫፎች ተደራሽ በማድረግ ላይ ነው።

የግብርና ግብዓቶችና የእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦት እና አገልግሎቶች

ምርጥ ዘር

በሀገር ደረጃ በምርጥ ዘር አቅርቦት ፋና ወጊ የሆነው ኮርፖሬሽኑ፣ በተለያዩ ክልሎች የራሱን ስድስት የምርጥ ዘር ማባዣ እርሻ ልማት ጣቢያዎችን በማቋቋም እንዲሁም በሰፋፊ የመንግሥትና የግል እርሻዎች እና በክላስተር በተደራጁ አርሶ አደሮች ማሳ በኮንትራት በመስራት በአጠቃላይ ከ20 ሺህ ሄክታር በሚበልጥ መሬት ላይ የ22 ሰብሎችን 90 ዝርያዎች እያባዛ በዓመት ከ400 ሺህ ኩንታል በላይ ዘር ለተጠቃሚዎች እያቀረበ ይገኛል። ይህም በሀገር ደረጃ ካለው የምርጥ ዘር ፍላጎት ውስጥ 30 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ እንዲያሟላ አስችሎታል።

በአጠቃላይ ኮርፖሬሽኑ በተለያዩ ክልሎች በአገኛቸው ተጨማሪ የእርሻ መሬቶች ዘር እያባዛ ሲሆን፣ ወደ ውጭ የሚላኩ ሰብሎችን ለማምረትም ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል።

ማዳበሪያ፣ አግሮኬሚካልና የእንስሳት መድኃኒት

ኮርፖሬሽኑ በሀገር ውስጥ ብቸኛ የጠጣር የአፈር ማዳበሪያ አስመጪ ሲሆን፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የአፈር ማዳበሪያዎች (በጠጣርና በፈሳሽ መልክ)፣ ጸረ አረም፣ ጸረ ነፍሳትና ጸረ ፈንገስ ኬሚካሎች እና የእንስሳት መድኃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚዎች በማቅረብ ላይ ነው።



የእርሻ መሣሪያዎች

ኮርፖሬሽኑ ለሀገሪቱ መልክአ ምድር እና የአየር ንብረት ተስማሚ የሆኑ ዘመናዊና ጥራት ያላቸውን ትራክተሮችና ተቀጽላዎች/ implements - ማረሻ፣ መከስከሻ፣ መስመር ማውጫ፣ ዘር መዝሪያ፣ ማዳበሪያ መበተኛ.../፣ ኮምባይን ሀርቨስተር እንዲሁም የኮንስትራክሽን እና የኬሚካል መርጫ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎችን ያቀርባል።

STIHL
SG 20

SHANTUI
SE380LC

SHANTUI
SHANTUI
SHANTUI

የሜካናይዜሽን አገልግሎት

የተቀናጀ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎትን በሁሉም የሀገሪቷ አካባቢዎች ተደራሽ በማድረግ የሚታወቀው ኮርፖሬሽኑ በግብርናው ዘርፍ ለተሰማሩ አርሶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች፣ ባለሃብቶች፣ የልማት ድርጅቶች ወዘተ ከመሬት ዝግጅት እስከ ጎተራ የሚዘልቁ የግብርና ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

የተቀናጀ የግብርና ግብዓትና የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከል

ኮርፖሬሽኑ ለካፒታል ፕሮጀክት በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት የዘር ማበጠሪያና የሜካናይዜሽን አገልግሎት ተደራሽ ባልሆነባቸው ክልሎች የተቀናጀ የግብርና ግብዓትና የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከል ለማቋቋም እየሰራ ነው፡፡ ለአብነት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በቦንጋ ከተማ የአስገነባውን ግዙፍ ማዕከል መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ ይህን መሰል ማዕከል በሌሎች ክልሎችም ለማስፋፋት የሚያስችል እንቅስቃሴ እያደረገ ነው፡፡

የቦንጋ የተቀናጀ የግብርና ግብዓት እና የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከል

የእርሻ መሣሪያዎችን የመገጣጠም ሥራ

የግብርና ሜካናይዜሽንን በማስፋፋት ረገድ ኮርፖሬሽኑ አዳዲስ የእርሻ መሣሪያዎችን ታዋቂ ከሆኑ የአውሮፓ እና የቻይና አምራች ኩባንያዎች በማስመጣት እና ባለው ወርክሾፕ በሂደት ሙሉ በሙሉ ገጣጥሞ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ ከውጭ ኩባንያዎች ጋር በሽርክና መስራት የሚችልበትን ስምምነት እያደረገ ነው። በአሁኑ ወቅት ተቋሙ የእርሻ መሣሪያዎችን በከፊል የመገጣጠም ሥራ እያከናወነ ይገኛል።

የደን ውጤቶች

ኮርፖሬሽኑ የደን ውጤቶች የሆኑትን ሙጫ፣ እጣን፣ ከርቤና አበከድ በማምረት እና በግዥ በማሰባሰብ አበጥሮ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ ጭምር በማቅረብ በዓመት በሚሊየን የሚቆጠር የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ላይ ነው።

ተቋሙ እነዚህን ምርቶች የሚሰበስበው በዘርፉ ከተሰማሩ ማኅበራትና ግለሰቦች በግዥ መልክ ሲሆን፣ የደን ውጤቶቹ በአብዛኛው በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በኦሮሚያ እና በሶማሌ ክልሎች ቆላማ አካባቢዎች ይገኛሉ።

የደረቅ ጭነት ትራንስፖርት እና የተሽከርካሪዎች ጥገና አገልግሎቶች

ኮርፖሬሽኑ ከባድ ተሽከርካሪዎችን በማሰማራት ለውስጥ እና ለውጭ ደንበኞች የግብርና ግብዓቶችን እና የእርሻ መሣሪያዎችን እንዲሁም ሌሎች የደረቅ ጭነቶችን የማንገዝ አገልግሎት ይሰጣል።

በሌላ በኩል ለውስጥ እንዲሁም ለተለያዩ የግልና የመንግሥት ተቋማት ደንበኞች የተሽከርካሪዎች የቅድመ መከላከል (Preventive Maintenance Service) እና የብልሽት ጥገና አገልግሎት (Maintenance Service) ይሰጣል።

በተጨማሪም ለከባድ እና ቀላል ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ምርመራ/ቦሎ/ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።

የዓመታዊ ሽያጭ፣ ትርፍና የተፈቀደ ካፒታል እድገት

ኮርፖሬሽኑ ባለፉት ዓመታት በሀገራዊ የግብርና ዘርፍ የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ እና ለሦስተኛ ጊዜ በአዘጋጀው የተቋሙ ስትራተጂክ ዕቅድ (ከ2016-2020 ዓ.ም) እየተመራ ውጤትን መሰረት ያደረገ የዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ሥርዓትን (BSC) የለውጥ መሣሪያ አድርጎ ወደ ሥራ በመግባቱ፣ በየዓመቱ በIFRS ደረጃዎች መሰረት በወቅቱ ሒሳብ በመዝጋቱና በማስቀጠሉ እንዲሁም የISO 9001:2015 የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓትን በመተግበሩ አበረታች ውጤት ማስመዝገብ ችሏል።

በዚህም ዓመታዊ ገቢውን ሲቋቋም ከነበረበት ከ1.4 ቢሊዮን ብር በ2016 በጀት ዓመት ወደ 10.76 ቢሊዮን ብር እንዲሁም ከታክስ በፊት ትርፉን ከ45.6 ሚሊዮን ብር በ2016 በጀት ዓመት ወደ 1.8 ቢሊዮን ብር ማሳደግ ችሏል። ከዚህ የተነሳ ኮርፖሬሽኑ በየዓመቱ ምርቱን እያሳደገ እና አገልግሎቶቹን ይበልጥ ተደራሽ እያደረገ በመቀጠሉ እንዲሁም ትርፋማ ሆኖ በመዝለቁ ምክንያት ሲቋቋም በመንግሥት የተፈቀደለትን 2.44 ቢሊዮን ብር ካፒታል በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በማሟላት አሁን ላይ የተፈቀደ ካፒታሉን ወደ 7 ቢሊዮን 564 ሚሊዮን ብር ማሳደግ ችሏል። የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎም የተቋሙን ካፒታል በድጋሚ ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ነው።

ማኅበራዊ ኃላፊነት

ማኅበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ ኮርፖሬሽኑ በየዓመቱ በአማካይ ለ2500 ዜጎች ጊዜያዊ የሥራ እድል እየፈጠረ ሲሆን፣ ከሚያገኘው ትርፍ ላይም በየዓመቱ ለማኅበራዊ አገልግሎት በጀት በመመደብ በምርጥ ዘር ማባዣ እርሻ ልማት አካባቢዎች ለሚገኘው ማኅበረሰብ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ በመንግሥት ለሚቀርብለት የተለያዩ የድጋፍ ጥሪዎች እና የስፖንሰርሺፕ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ሲሰጥ ቆይቷል፤ አሁንም ድጋፍ ማድረጉን ቀጥሏል።

በዚህ መሰረት በበጎ አድራጎት ሥራዎች በእርሻ ልማቱ አካባቢዎች ለሚገኘው ማኅበረሰብ ትምህርት ቤት በመገንባት፣ መብራት በማስገባት፣ የአቅመ ደካሞችን መኖሪያ ቤቶች በማደስ፣ ለችግረኛ ቤተሰብ ልጆች

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በመለገስ፣ መንገድ በመስራት እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች ችግኞችን በመትከል፣ ደም በመለገስ ወዘተ ድጋፍ እያደረገ ነው። በተመሳሳይ ለአካባቢው አርሶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች በአምስት በመቶ የዋጋ ቅናሽ ምርጥ ዘር በማቅረብ ለአርሶ እና አርብቶ አደሩ ያለውን አለኝታነት በማረጋገጥ ላይ ይገኛል።

የአቅመ ደካማ ቤቶች ግንባታ በባሌ ሮቤ እና በአዲስ አበባ

በጦርነት ፈርሶ የነበረው የውቅሮ ማራይ ት/ቤት ግንባታ - ትግራይ ክልል

እውቅና እና ሽልማት

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ኢግሥኮ) በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በሚያቀርባቸው የግብርና ግብዓቶችና በሚሰጣቸው የተቀናጁ አገልግሎቶች በገበያ ውስጥ ተመራጭ ስለመሆኑ የረጅም ዓመት ደንበኞቹ ምስክሮች ናቸው።

ኮርፖሬሽኑ በግብርናው መስክ በአስመዘገበው አበረታች ውጤት የአቢሲኒያ ዓለም አቀፍ የጥራት ድርጅት ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለኢንደስትሪ ሽልማት ካጫቸው ከ57 ሺህ በላይ አምራች እና አገልግሎት ሰጪ የመንግሥት፣ የግል እና ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ውስጥ ከተመረጡ 50 ተቋማት አንዱ በመሆን መጋቢት 2015 ዓ.ም የመጀመሪያውን የኢንደስትሪ የከፍተኛ ክብር ሽልማት ተቀዳጅቷል።

በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ በ2016 በጀት ዓመት ከ743 ሚሊየን ብር በላይ ግብር በመክፈል ለሁለተኛ ጊዜ በታማኝ ግብር ከፋይነት በፕላቲነም ደረጃ ከኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እጅ ሽልማት ተቀብሏል።

ከዚህ ባሻገር በ2015/16 የምርት ዘመን በሀገር አቀፍ ደረጃ በስንዴ ልማት ከሀገራዊ ፍላጎት እስከ ውጭ ገበያ አቅራቢነት በመሸጋገር ሂደት ለአበረከተው የላቀ አስተዋጽዖ እንዲሁም በ2016/17 ምርት ዘመን የአፈር ማዳበሪያ ግዥ፣ አቅርቦት እና ሥርጭት እንዲሳለጥ ለተወጣው ከፍተኛ ድርሻ የእውቅናና የምስጋና የምስክር ወረቀቶች እና ዋንጫ አግኝቷል።

በሌላ በኩል የኮርፖሬሽኑ የወንዶች የመረብ ኳስ ቡድን የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮ) በ2015 ዓ.ም በአዘጋጀው የስፖርት ውድድር ሻምፒዮን በመሆን የዋንጫ ተሸላሚ ሆኗል።

የምስጋና
የምስክር ወረቀት

ለ ኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን

በሀገር አቀፍ ደረጃ በስንዴ ልማት ከሀገራዊ ፍላጎት እስከ ውጭ ገበያ አቅራቢነት
በመሸጋገር ሂደት ላበረከቱት የላቀ አስተዋፅኦ ይህ የምስክር ወረቀት
ከምስጋና ጋር ተሰጥቷል።

ቀኑ 01/2016 ዓ.ም

Certificate of Recognition
የምስጋና የምስክር ወረቀት

This certificate of recognition and appreciation is awarded
To Ethiopian Agricultural Business Corporation
By the FDRE Ministry of Agriculture in recognition of your outstanding contributions to facilitating the procurement process of soil fertilizer during the 2023/24 crop season.

Date Issued

Beyond Production

አደረጃጀት

የአርሶና አርብቶ አደሩ አለኝታ የሆነው የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ኢግሥኮ) በመንግሥት የተሰጠውን ተልዕኮ ከመወጣት አኳያ በአራት ኮርፖሬት ዘርፎች፣ ዓላማ አስፈጻሚ በሆኑ አምስት የኦፕሬሽን ዘርፎች፣ በ14 ድጋፍ ሰጪ የሥራ ሂደቶች እንዲሁም በበርካታ ቅርንጫፎች እና ጣቢያዎች በተደራጀ መዋቅር በ1,363 ቋሚና በ272 ኮንትራት በድምሩ በ1,635 ሠራተኞች ግብርናን ለማዘመን እየሰራ ይገኛል።

የዘርፎች አድራሻ እና የሚሰጡት አገልግሎት

ምርጥ ዘር፣ የዘር ብጠራ አገልግሎት፣ የአፈር ማዳበሪያ፣ አግሮኬሚካል፣ የእንስሳት መድኃኒትና የኬሚካል መርጫ መሣሪያዎች ካስፈለግዎ

የግብርና ግብዓት ምርትና አቅርቦት ዐቢይ ዘርፍ

ስልክ፡- +251-11-440-3610
ፋክስ፡- +251-11-442-3613

ለምርጥ ዘር አንዲሁም ለዘር ብጠራ አገልግሎት

የምርጥ ዘር አቅርቦት ዘርፍ

ስልክ፡- +251-11-661-2266
ፋክስ፡- +251-11-618-6123

ለአፈር ማዳበሪያ፣ አግሮኬሚካል፣ እንስሳት መድኃኒትና የኬሚካል መርጫ መሣሪያዎች

የግብርና ግብዓት አቅርቦት ዘርፍ

ስልክ፡- +251-11-442-5623/28
ፋክስ፡- +251-11-442-5622

የእርሻ መሣሪያዎች፣ የጭነት ተሽከርካሪዎችና ጥገና፣ የግብርና ውጤቶች ሽያጭና የሜካናይዜሽን አገልግሎት ቢያስፈልግዎ

የእርሻ መሣሪያዎች እና የግብርና ውጤቶች አቅርቦት ዐቢይ ዘርፍ

ስልክ፡- +251-11-442-5012

ለአስተማማኝና ዘመናዊ የእርሻ እና የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ሽያጭና ኪራይ፣ መለዋወጫ እንዲሁም የቴክኒክ ሥልጠና አገልግሎት

የእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦት ዘርፍ

ስልክ፡- +251-11-442-3438
ፋክስ፡- +251-11-442-0895

ለመሬት ዝግጅት፣ ምንጣሮ፣ መሬት ድልዳሎ፣ ለእርሻ ሥራ፣ ሰብል ለመሰብሰብና ለመውቃት እንዲሁም ለዕጣን፣ ሙጫ፣ ከርቤና አበከድ አቅርቦት

የግብርና ውጤቶች ሽያጭና የሜካናይዜሽን አገልግሎት ዘርፍ
ስልክ፡- +251-11-442-5012

ለደረቅ ጭነት አገልግሎት እንዲሁም ለእርሻ መሣሪያዎችና የቀላል ተሽከርካሪዎች ጥገና

የተሽከርካሪዎች አስተዳደርና ጥገና ዘርፍ
ስልክ፡- +251-11-470-8470
ፋክስ፡- +251-11-442-0434

የሰው ሀብት፣ የግዥና ንብረት እንዲሁም የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ መረጃዎች ቢያስፈልግዎ

ኮርፖሬት ሀብት አመራር ዘርፍ
Tel: +251-11-442-1213
Fax: +251-11-442-2314

ግብርናን ማዘመን ግባችን ነው!

Ethiopian Agricultural Businesses Corporation (EABC)

Company Profile

Establishment of EABC

The Ethiopian Agricultural Businesses Corporation (EABC) was established in December 2015 as a federal government public enterprise under Council of Ministers Regulation No. 368/2015, with an authorized capital of 2.44 billion birr.

The Corporation, governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992, was formed through the merger of five-state owned Enterprises; namely Ethiopian Seed Enterprise, Agricultural Inputs Supply Enterprise, Agricultural Equipment and Technical Services Share Company, Agricultural Mechanization Service Enterprise, and Natural Gum Processing and Marketing Enterprises.

Currently, the Corporation, which has several branch offices and six improved seed multiplication farms for various crops in different regions, is accountable to Ethiopian Investment Holdings and is also governed by a board of directors that supervises and controls the operations and business of the EABC as well.

At present, EABC is playing its part in the implementation of the 10- year master plan for the agricultural sector at a national level. Based on this, it carries out agricultural activities ranging from land preparation to warehouse by providing integrated services through a single window, including agricultural inputs and mechanization services. In this regard, the Corporation supplies:

- Improved Seeds
- Solid and Liquid (including foliar) Fertilizers
- Agrochemicals and

- Veterinary Drugs to customers at affordable prices.

And also, the Corporation is striving to achieve its mission by rendering the following services:

- Agricultural Machinery with Original Spare Parts and Implements
- Construction Equipment
- Chemical and Fertilizer Spraying Machines
- Agricultural Mechanization Services
- Land development service
- Seed Cleaning Service
- Repair Services for Agricultural and Construction Equipment
- Rental Services for Agricultural Machinery and Transport Vehicles (heavy goods transportation)
- Maintenance, Consulting, Technical/Vocational Training at the head office and its branches, along with after-sales service.

Additionally, Assembling Agricultural Equipment is also listed among the Corporation's duties and responsibilities.

Furthermore, EABC is mandated to harvest, purchase, add value to, and process natural gum (GUM Arabic), as well as produce other forest products such as Gum Olibanum, Gum Myrrh & Gum Opoponex, supplying them to both domestic and international markets.

Since its establishment, the Corporation has achieved remarkable success in the agricultural sector. Building on these promising results, EABC has continued to play a vital role in modernizing agriculture, boosting production and productivity.

As a testament to its progress, the Corporation successfully met its authorized capital within a five-year period and a significant milestone that highlights its achievements in recent years. Its capital has now reached 7.564 billion birr.

Overall, the Corporation is making significant contributions to modernizing agricultural practices and enhancing productivity through integrated agricultural development activities, from land preparation to warehouse. And also by implementing the ISO 9001:2015 quality management system, the Corporation has achieved significant and encouraging results.

Purposes of establishment

The purposes for which the Corporation is established are:

1. to buy from domestic and international markets and supply agricultural inputs; undertake agricultural inputs market price stabilization activities;

2. to render agricultural mechanization services, agricultural and construction equipment repair services and provide rental services of agricultural machineries and transport vehicles;

3. to buy from domestic and international markets and supply agricultural machineries and spare parts, construction equipment and agro-chemicals;

4. to provide necessary education for the promotion of the use of modern agricultural machineries; provide consultancy service in handling and use of agricultural machineries and provide on the job technical trainings;

5. to harvest, buy, value add to and process natural gum, produce other forest products, and supply to domestic and international markets;

6. to undertake agricultural land development studies and preparation of designs, agricultural land surveying, clearing, leveling, drainage and irrigation activities as well as other activities related to agricultural land development;

7. to cause undertaking of feasibility studies, design preparation, technology selection and negotiation, erection and commissioning of new and expansion projects as well as for research activities;

8. to cause the local designing and manufacturing of agricultural machineries and spare parts in partnership with capable local and foreign companies;

9. to work in cooperation with the concerned educational research and training institutions in producing trained manpower in such fields, numbers and quality as required by the sector;

10. to undertake studies, based on direction given to it by the Ethiopian Investment Holdings, for the acquisition of financial, technological and modern governance inputs (including attracting investments or participating in investments) that can help it to become competitive, both locally and globally, and profitable and implement same upon approval;

11. to multiply, clean and process pre-basic, basic and certified seeds of various crops, vegetables and fruits; where necessary import pre-basic seeds and cause their production or sale them; to sell byproducts;

12. to undertake research and implement improvements with respect to the supply of agricultural inputs, agricultural machineries repair, the production and marketing of natural gum, mechanization services and related matters and thereby ensure its competitiveness;

13. to sell bonds, collateralize, negotiate and sign loan agreements with local and foreign sources in accordance with directives issued by the Ministry of Finance and on the basis of the guidance of Ethiopian Investment Holdings;

14. to engage in other related activities for the attainment of its purposes.

EABC's mission, vision & values

Mission

Provide agricultural inputs and technologies that can significantly improve production and productivity, enhance modern farms and agro-industries at very competitive price to accelerate the nation's economic development.

Vision

By providing integrated agricultural inputs and mechanization service, to become a strong competitor in Africa by 2030.

Values

- Loyalty
- Transparency
- Sincerity
- Commitment
- Mutual benefit
- Social responsibility

The products and services of EABC

Products

Improved seeds: EABC multiplies and supplies 22 crop species and 90 varieties to farmers, semi-pastoralists, investors and institutions.

Improved seeds

Forest products: The Corporation offers forest products, including natural gum (GUM Arabic), Gum Olibanum, Gum Myrrh & Gum Opoponex for both local and international markets.

Fertilizers: EABC imports and distributes solid and liquid (including foliar) fertilizers to customers.

Agrochemicals and Chemical spraying equipment: The Corporation supplies herbicides, pesticides, fungicide, disinfectants and chemical spraying equipment.

Agricultural equipment, construction machinery and spare parts: The Company provides reliable and modern agricultural machinery and spare parts such as tractors, combine harvesters, furrowers, disc plows, tyres, inner tubes, batteries, filters, copper wires etc. It also offers construction machinery.

Agricultural Equipment

Tractor

Combine Harvester

Chemical Sprayer

Disc Harrow

Services

Mechanization

Land Development

Services

- Integrated Agricultural Mechanization Services
- Land development service
- Seed Cleaning Services
- Maintenance Services for Farm Equipment, Trucks, Vehicles, and more
- Sales and Rental Services for Farm Equipment and Construction Machinery
- Heavy Goods Transport Rental Services
- Consultancy, Technical Training and Maintenance services to its customers along with after-sales services.

Human resource

The corporation currently employs a total of 1,635 staff members, comprising 1,363 permanent employees and 272 are contract workers.

Organizational Structure

EABC is mainly organized into four sectors:

1. Agricultural Input Product and Supply Main Sector
2. Agricultural Machineries and Products Supply Main Sector
3. Corporate Resource Management Sector
4. Chief finance office

These sectors are accountable to the Chief Executive Officer of the Corporation. Additionally, the organization includes five business units at the head office as well as several branch offices and stations located in various regions of the country, all operating under the main sectors.

There are also 14 support units with distinct functions within in the organization.

The Address of EABC's Head Office, along with its Main Sectors and Business Units

Ethiopian Agricultural Businesses Corporation

City: Addis Ababa
Sub city: Akaki Kality
District/Wereda: 06 - (Saris area)
Street: On the main road to Kality adjacent to Equatorial Business Group P.L.C or FAFFA Food S.C
Tel: 0114 424177/84
P.O.BOX: 6898
Email: info@ethioagri.com or ethioagribusco@gmail.com
Website: www.ethioagri.com
Facebook: Ethiopian Agricultural Businesses Corporation

Corporate Communication and Social Responsibility Department

Tel: +251-114 42 41 25
Fax: +251-114 42 13 12

Agricultural Inputs Product and Supply Main Sector
Tel: +251-11-440-3610
Fax: +251-11-442-3613

For various improved seeds and seed cleaning service, please contact

Seeds Supply Sector
Tel: +251-11-661-2266
Fax: +251-11- 618- 6123

If you need solid & liquid (including foliar) fertilizers, agrochemicals, chemical spraying equipment and veterinary drug, please contact

Agricultural Inputs Supply Sector
Tel: +251-11-442-5623/28
Fax: +251-11-442-5622

Agricultural Machineries and Products Supply Main Sector
Tel: +251 114 42 50 12

If you are looking for farm equipment, construction machineries, spare parts, and technical training, please contact

Agricultural Equipment Supply Sector
Tel: +251-11-442-3438
Fax: +251-11-442-0895

If you are seeking integrated mechanization service and incense, myrrh and gum, please contact

Agricultural Products Sales and Mechanization Service Sector
Tel: +251 114 42 50 12

If you need rental services for transporting goods and farm equipment as well as vehicle maintenance, please contact

Trucks Administration and Maintenance Sector
Tel: +251-11-470-8470
Fax: +251-11-442-0434

If you need services related to human resources, procurement, property, as well as information and technology, please contact us.

Corporate Resource Management Sector
Tel: +251-11-442-1213
Fax: +251-11-442-2314

Modernizing agriculture is our goal!

ETHIOPIAN AGRICULTURAL BUSINESSES CORPORATION
ETHIOPIAN AGRICULTURAL BUSINESSES CORPORATION

Liquid fertilizers